# የሙዝ ልጣጭ



1ኛ ክፍል
29-30ኛው ሳምንት
መጽሐፍ 16

# የሙዝ ልጣጭ

መጽሐፍ 16 | 1ኛ ክፍል | 29-30ኛው ሳምንት



ይህ አጋዥ የንባብ መጽሐፍ ከዩ.ኤስ.ኤ.አይ.ዲ. (USAID) በተገኘ የገንዘብ ድጋፍ በፓክት ኢትዮጵያ (Pact Ethiopia) እና በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ትምህርት ቢሮ የጋራ ትብብር ተዘጋጅቶ በሴቭ ዘ ቺልድረን (Save the Children) እና በትምህርት ሚኒስቴር ተሻሽሎ ታተመ::

The CC By license lets others distribute, adjust, and build upon this work, for free or commercially, as long as credit is given to the original creation. However, any changes from the original must be indicated.
For more info please refer: *https://creativecommons.org/licenses/*



ሙዝ መብላት በጣም
እወዳለሁ።

እናቴ የሰጠችኝን ሙዝ
ልጬ ዋጥ ዋጥ
አደረከኩት፡፡ ቤተሰቦቼም
ድርሻቸውን በሉ፡፡ ልጣጩን
ወርውሬ ጨዋታዬን
ቀጠልኩ፡፡



ስጫወት ቆየሁ። ውሃ
ጠማኝ። ውሃ በብርጭቆ
ቀዳሁ፤ ብርጭቆውን
ወደአፌ እንዳስጠጋሁ
ራመድ አልኩ። አንሸራቶኝ
ወደቅኩ። ብርጭቆው
ተሰባበረ።



ጥሜን ሳላረካ ቀረሁ:: ለመነሳት ሞከርኩ:: ሙዙ እንደገና አንሸራቶ ጣለኝ:: አለቀስኩ::



እናቴ ለቅሶዬን ሰምታ
እየሮጠች መጣች:: አጠገቤ
ስትደርስ እሱዋም አድጦአት
ወደቀች:: ዋይ! አለች::



አባቴ ድምፁዋን ሰምቶ እየሮጠ መጣ:: የሙዙን ልጣጭ ስላላየው እሱም አድጦት ወደቀ:: የሙዝ ልጣጭ ሶስታችንም ከወለሉ ላይ አገናኘን::

እናቴ አካባቢውን ተመለከተች። ሶስታችንንም የጣለን የሙዝ ልጣጭ መሆኑን ተረዳች። ሌላ ጊዜ የሙዝ ልጣጭ በቆሻሻ ማጠራቀሚያ እንድጥል መከረችኝ።



ብዙ ጉዳት አልደረሰም::
እናቴ ፈጣሪዋን አመሰገነች::

USAID

ከአሜሪካን ህዝብ